# ፓስተር ማስረሻ 11/11/18

ደቀ-መዝሙርነት



ማቴዎስ 28 (Matthew)
16፤ አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸው
ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፥
17፤ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ።
18፤ ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡— ሥልጣን ሁሉ

በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።
19-20፤ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።
በምድር ላይ ሊጠፉ የተቃረቡ ፍጥረታት በባለሙያዎች አጠራር in danger ይባላሉ ፣ ዛሬ በቤተ/ክ ውስጥ ሊጠፉ ከተቃረቡ አስተምህሮቶች አንዱ ደቀ - መዛሙር የሚባለው ትምህርት ነው።
ነገር ግን የጌታ ቃል ቅዱሳን ሁሉ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ እና ሌሎችን ደቀመዝሙር ለማድረግ ነው የተጠራነው።
በአዲስ ኪዳን ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል ከ 260 ጊዜ በላይ ተደጋግሞ ተጠቅሷል።
በብሉይ ከሶስት ጊዜ በላይ አልተጠቀሰም።
ኢሳ 54:13
ደቀ መዝሙር ማለት :-
ከመምህሩ የተማረ ፣ የመምህሩ ተከታይ፣ ልክ እንደመምህሩ የሆነ ማለት ነው።
ዛሬ ሰው ሁሉ ምን መሆን ትፈልጋለህ? ተብሎ ቢጠየቅ አገልጋይ መሆን ይፈልጋል።
እግዚአብሔር ግን ደቀ መዝሙር እንድንሆን ነው የሚፈልገው።
እውነተኛ ደቀ - መዝሙርነት ሁለንተናን መስጠት ነው ፣ ሁለንተናን መስጠት ።
ሮሜ 12:1 - 2 .....በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ።
ዛሬ ቤተ/ክ ተሀድሶ ያስፈልጋታል፣ ዓለማዊነት ቤተ/ ክ ውስጥ ገብቷል ፣ እውነተኛ ደቀመዝሙርነት ስለጠፋ ዓለም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነግሷል።
ዮሐንስ 8 (John)
31፤ ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ፦— እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤

32፤ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል፡ አላቸው።
#አማኞች ነበሩ  ደቀ መዛሙርት ግን አልነበሩም።
#አማኝ ተሁኖ ደቀ መዝሙር ልይኮን ይቻላል።
በፈሪሳውያንና በዓለማውያን ዘንድ ደቀ መዛሙርትነት ነበር፣
ፈሪሳውያን የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነንሸየሉ ነበር ፣ ብዙ ፈላስፎችም ደቀ መዛሙርት ነበሯቸው።
***አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን ሆኖ ደቀ መዝሙር ሳይሆን ዘመኑን ሊጨርስ ይችላል።***
ደቀ መዝሙርነት በአዕምሮ መታደስ መለወጥ ነው።
ደቀ መዝሙርነት ጥሪ ነው።
ማቴዎስ 10 (Matthew)
1፤ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እንዲያወጡአቸው በርኵሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።
ሉቃስ 6 (Luke)
13፤ በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤
***ደቀ መዝረሙርነትን የሚበልጥ በረከት ወይም የፀጋ ስጦታ የለም ከጥሪዎች ሁሉ የከበረ ጥሪ ነው***
እግዚአብሔር በራሱ አሰራር ደቀ መዛሙርት እንድንሆን መረጠን።
ለዚህ ጥሪ ምላሽ ሰጥተሀል ወይ???
ደቀ መዝሙርነት ጥሪ ነው ስንል
1ኛ, ከእርሱ ጋር እንድንኖር( አብሮነት)።
ማርቆስ 3 (Mark)
13፤ ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።
14፤ ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥
****አብሮነት ከጌታ ጋር 24/7 ፣ከምንጨ ጋር ተጣብቀን እንድንኖር ጌታ ጠርቶናል***
2ኛ, ለተልዕኮ ነው የተጠራነው።

ይቀጥላል ..........

Last modified: 1:25 PM